# ምእራፍ ሶስት

# የተውኔት መዋቅር

የተውኔት መዋቅር በገቢርና በትእይንት እየተከፋፈለ ይቀርባል።

## 3.1. ገቢር

ገቢር የተውኔት አቢይ ክፍል ወይም ምእራፍ ነው። ተውኔትን በገቢር የመከፋፈሉ ዘዴ የተገኘው ከግሪክ ዘመን አይሽሬ ተውኔቶች ነው ተብሎ ይገመታል። የገቢር አከፋፈል የሚያስፈልግበት ሁለት ምክንያቶች አሉ። የመጀመሪያው በውሱን ቦታና ጊዜ ተከታታይ ድርጊትን ማሳየት ስለሚያዳግት ታሪኩን ደረጃ በደረጃ ለማቅረብ እንዲቻል ሲባል ነው። ሁለተኛው ደግሞ በተከታታይ ያለ እረፍት የሚቀርብ ታሪክ ለተመልካች አሰልቺ ሊሆን ስለሚችል ነው።

በተውኔት ታሪክ ውስጥ ያሉ ድርጊቶች በሙሉ በመድረክ ላይ ሲታዩ በተመሳሳይ ጊዜና ቦታ እስከ ፍጻሜው ድረስ አንድ ላይሆን ይችላል። ይህም በመሆኑ የመቼት ለውጥ አስፈላጊ ሆኖ ይገኛል። ይህንም የመቼት ለውጥ ለማመልከት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች (ለምሳሌ የመድረኩ መልክ፣ ቁሳቁሶች፣...) ይለወጣሉ። ይህን ለማድረግ ለተወሰኑ ሰከንዶች/ደቂቃ/ መጋረጃ ይዘጋል። ይህን የለውጥ ሂደት ነው ገቢር ብለን የምንጠራው።

በተውኔት ውስጥ የገቢር መጠን ተውኔቱ እንደተጻፈበት ዘመንና የታሪክ ስፋት የሚወሰን ነው የሚሆነው። በኤልሳቤጣውያን ጸሀፌ

ተውኔቶች ዘመን በአምስት ገቢሮች የመከፋፈል ልማድ ነበረ። በ19ኛው ክፍለ ዘመን ደግሞ በባለ አራት ገቢር ተውኔት መጻፍ ተጀመረ። ከዚያም ቀስ በቀስ በባለ ሶስት ገቢር ተውኔት መጻፍ የተሻለ ተቀባይነት እያገኘ መጣ። በዚህ ዘመን ደግሞ የሙሉ ጊዜ ተውኔት ደራሲያን የተውኔታቸውን ገቢር ቢያንስ በሁለት፣ ቢበዛ ደግሞ በሶስት የገቢር መጥነው በመጻፍ ያቀርባሉ።
ከዘመን በተጨማሪ የተውኔቱ ታሪክ ስፋትና ጥበትም ተውኔትን በገቢር ለመከፋፈል መነሻ ሊሆን ይችላል። በመሆኑም እንደታሪኩ ስፋትና ጥበት አንድና ከአንድ በላይ በሆኑ ገቢሮች ሊከፈል ይችላል።

## 3.2. ትዕይንት

ትእይንት የገቢር ንኡስ ክፍል ነው። በአብዛኛው አንድ ገቢር በትእይንት የሚከፈለው የጊዜ ለውጥ ሲኖር ነው። አልፎ አልፎ ደግሞ በዚያው መቼት ውስጥ የቦታ ለውጥ ሲኖር (ለምሳሌ፣ ከሳሎን ወደ መኝታ ቤት፣ ከመኝታ ክፍል ወደ ውጭ፣...) ሊሆን ይችላል። የትእይንት ክፍፍልን የመብራት ጥበብን በመጠቀም መከወን ይቻላል። ይህም ሲባል መብራቱን ላጭር ጊዜ እንዲጠፋ በማድረግ የተፈለገውን ለውጥ ማካሄድ ማለት ነው።

ስለገቢርና ትእይንት መገንዘብ ያለብን ጉዳይ አለ። ይኸውም በገቢርና በገቢር፣ በገቢርና በትእይንት፣ እንዲሁም በትእይንትና በትእይንት መካከል የጠበቀ ቁርኝት መኖሩ ልብ ሊባል ይገባል።

አንዱ ወደሌላው የሚሸጋገር ሆነው ካልቀረቡ የታሪኩን አንድነትና ግጥምጥምነት ያላላል። ስለዚህ ታሪኩ ተከታታይነቱን ጠብቆ እንዲቀጥል የእነዚህ ክፍሎች የእርስ በእርስ ትስስር መዘለል የለበትም።

## 3.3. ማስተዋወቂያ

ማስተዋወቂያ ለገጸባህሪያቱ ማንነት፣እርስበርስ ስላላቸው ግንኙነት፣ ስላሉበት ሁኔት፣ ወዘተ. ፍንጭ መስጫ ነው። ማስተዋወቂያ የትም ቦታ ይገኝ ዋና ተልእኮው ገጸባህሪያቱን ማስተዋወቅ ነው። ነገር ግን ማስተዋወቂያ ወሳኝ ጉዳይ ቢሆንም ሁሉንም ዘርግፎ የሚያመጣ መሆን የለበትም። ፍንጭ ከመስጠት አልፎ አይሄድም።

የማስተዋወቂያ አላማ ለታዳሚያን ጥቆማ መስጠት ነው። በዚህ ክፍል ታሪኩ የሚፈጸምበት ቦታ፣ ወቅት፣ የገጸባህሪ ማንነት፣... ይጠቆምበታል። ታሪኩ በመድረክ ላይ ከመታየቱ በፊት የሆኑ ድርጊቶችም በዳራነት ሊቀርቡ ይችላሉ። ይህ ክፍለ በልቦለድ ንግር የሚባለው ነው።

በተውኔት መዋቅር ውስጥ ገጸባህሪያት የሚተዋወቁት በተለያየ መንገድ ሊሆን ይችላል። እነዚህ መንገዶችም ቀጥተኛና ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ሊከወን ይችላል። ቀጥተኛ የሆነው ማስተዋወቂያ ስልት ገጸባህሪያቱን በቀጥታ በመግለጽ የሚያቀርብ ነው። ይኸውም ገጸባህሪያቱ ምን እንደሚመስሉ ጸሀፊ ተውኔቱ

የሚገልጽበት ስልት ነው። በመሆኑም የገጸባህሪያቱ አካላዊና ህሊናዊ መልክ ይቀርባል።

ሊ-ቀጥተኛ የማስተዋወቂያ ዘዴ የምንለው ገጸባህሪያቱን በድርጊት የሚያሳይ ማስተዋወቂያ ነው። ይኸውም የገጸባህሪያቱን አመል፣ ንግግር፣ አስተሳሰብና አመለካከት፣ ሰብዕና እና ከሌሎች ገጸባህሪያት ጋር ያላቸውን ግንኙነት ከሚፈጽሟቸው ድርጊቶች የምንገነዘብበት ማስተዋወቂያ ነው።

ከነዚህ ሁለት ማስተዋወቂያዎች በተጨማሪ ሌሎች ሁለት የማስተዋወቂያ መንገዶች አሉ። እነዚህም ግለኛ መነባንብና ጎንዮሽ ናቸው። ግለኛ መነባንብ የሚባለው አንድ ገጸባህሪ ብቻውን በመድረክ ላይ በመታየት ለተመልካቹ ሃሳቡን የሚነግርበት ነው። በዚህ ንግግሩን፣ ማንነቱን፣ ምኞቱን፣ ስለሌሎች ገጸባህሪያት ያለውን አመለካከት፣... ይገልጻል።
ጎንዮሽ የሚባለው ደግሞ አንዱ ገጸባህሪ ከሌሎቹ ፈንጠር ብሎ በመውጣት ሌሎች እንዳልሰሙት በመቁጠር ለተመልካቹ የሚነገርበት ዘዴ ነው። በዚህ ጊዜ ስለሌሎች ማንነት፣ ወይም ከጉዳዩ ጋር ስላላቸው ግንኙነትም ሆነ አስተያየት እነሱን በማሳጣት ወይም ለተመልካቹ በማጋራት አይነት ያስተዋውቃል።